Washington State
Department of Social
& Health Services

*Transforming lives*

DEVELOPMENTAL DISABILITIES ADMINISTRATION (DDA)

# የቆዳ ምልከታ ፕሮቶኮሎች

## Skin Observation Protocols

**Client's Name and Address**

**Client Representative's Name and Address**

ውድ ፥

የDDA አጠቃላይ ምዘናና የሪፖርት ማድረጊያ ግምገማ መሳሪያን በመጠቀም የእንክብካቤና የአገልግሎት ፍላጎቶችዎን መገምገም በቅርቡ አጠናቅቄያለሁ። የእርስዎን የDD ግምገማ ሲያጠናቅቁ፣ ከእርስዎ ወይም ከእንክብካቤ ሰጪዎችዎ በተገኘው መረጃ፣ DDA የቆዳ እንክብካቤና የቆዳ ምልከታን በተመለከተ የእርስዎን እንክብካቤ ለማሻሻል ለእርስዎ ወይም ለእንክብካቤ ሰጪዎችዎ መረጃ ለመስጠት የሚያስችል ዕድል ለይቷል።

የDDA ግምገማዎ በግፊት፣ በእርጥበት፣ ባለመቻል ወይም ባለመንቀሳቀስ ምክንያት ለቆዳ መበላሸት አደጋ ሊጋለጡ እንደሚችሉ ወስኗል፣ ይህም ወደ ኢንፌክሽን አልፎ ተርፎም ለሞት ሊዳርግ ይችላል። ግምገማዎ ለቆዳ መበላሸት አደጋ ላይ እንዳሉ ሲወስን፣ DDA የቆዳ ምልከታ ፕሮቶኮልን (SOP) ይጀምራል። ይህ የቆዳ ግምገማን የሚያጠናቅቅ ወደ ነርስ ማስተላለፍን ያጠቃልላል። ከፈለጉ፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ አሁን ያሉበትን የቆዳ ሁኔታ በተመለከተ፣ በDDA በኩል በኮንትራት ከተያዘ/ች ነርስ ይልቅ፣ ደብዳቤ ሊያቀርብ ይችላል። የSOP ግምገማን ለማጠናቀቅ ነርስ ከመረጡ፣ የSOP ግምገማ ቀጠሮን ለማስያዝ **በአምስት (5) ቀናት** ውስጥ የጉዳይዎ ማናጀር እንድ ነርስ እንዲታነጋግሮት/እንዲያነጋግሮት ያድርጋል። ነርሱ/ሷ ከሁለት ሙከራዎች በኋላ ቀጠሮ ማስያዝ ካልቻለ/ች ወይም የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ አሁን ያለዎትን የቆዳ ሁኔታ የሚገልጽ ደብዳቤ ለDDA ካልሰጡ፣ የጉዳይዎ ማናጀር በህጻን ጥበቃ አገልግሎቶች ወይም በአዋቂዎች ጥበቃ አገልግሎቶች በኩል የግዴታ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅበታል።

አንድ ሰው በግፊት ምክንያት ለቆዳ መበላሸት አደጋ ሲጋለጥ በእርስዎ ወይም ለእርስዎ፣ ቆዳዎ ጤናማ ሆኖ እንዲቆይ ለማድረግ አንዳንድ መሰረታዊ እንክብካቤዎች አሉ። ለመከተል የሚያስፈልጉ የተወሰኑ አጠቃላይ ምክሮች እነዚህ ናቸው።

1. በመታጠብ ወይም በግላዊ እንክብካቤ ላይ እገዛ ከፈለጉ ሁሉንም ቆዳዎ እንዲመለከት የሚረዳዎትን ሰው በተለይም በሰውነትዎ ላይ ያሉትን የአጥንት ቦታዎችን በቆዳ መልክ ላይ ለሚደረጉ ለውጦች ማለትም የሙቀት መጠንን፣ ክፍት ቦታዎችን፣ ህመምን እና/ወይም ሽታዎችን እንዲመለከት ይጠይቁ።
2. እራስዎን መታጠብ ከቻሉ በመታጠቢያዎ ወቅት ለሚደረጉ ለውጦች ቆዳዎን ይፈትሹ፥ ይህም በቆዳዎ ገጽታ፥ ቀለም፥ ሙቀት፥ ክፍት ቦታዎች፥ ህመም እና/ወይም ሽታ ላይ ለውጦችን ያካትታል።
3. በቆዳዎ ገጽታ ላይ ስለሚደረጉ ለውጦች ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይነጋገሩ። በቆዳዎ ላይ ያልተለመዱ ወይም የማይመቹ የግፊት ቦታዎች ላይ ችግሮች ካጋጠሙዎት ያሳውቋቸው። ቆዳዎን እንዲመለከቱ ይጠይቋቸው። ቆዳዎን በሚመለከት ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት፣ ስለ ቆዳ እንክብካቤ ጥቆማዎች የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ይጠይቁ። የቆዳ መበላሸት ወይም የግፊት ጉዳት ካጋጠመዎት እርስዎና የእንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች አካባቢውን እንዴት እንደሚንከባከቡ መረዳታቸውን ያረጋግጡ።
4. ከዚህ ደብዳቤ ጋር ተያይዞ እርስዎና የእንክብካቤ ሰጪዎችዎ የቆዳ እንክብካቤና የግፊት ጉዳቶችን አስፈላጊነት እንዲገነዘቡ የሚያግዙ የትምህርት ቁሳቁሶችን ያገኛሉ።

ስለ ቆዳዎ እንክብካቤ ወይም የቆዳዎ ገጽታ ለውጦች ጥያቄዎች ካሉዎት ወዲያውኑ ለዶክተርዎ ወይም ለሌላ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ይደውሉ።

ስለዚህ መረጃ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ የእርስዎን DDA ጉዳይ/ ንብረት አስተዳደር፣ ፣ በ ላይ ያግኙ። ለተጨማሪ መረጃ እሱ/እሷ ወደ ነርስ ወይም ሌላ የጤና እንክብካቤ ምንጮች ይልክልዎታል።

ከሰላምታ ጋር፤

የDDA ጉዳይ/ የንብረት አስተዳዳሪ
አባሪ